# ሙጋቤና የዚምባብዌ ሕዝብ

**መስፍን ወልደ ማርያም**

**ታኅሣሥ 2001**

ፕሬዚደንት ሙጋቤ የብዙዎቹ የአፍሪካ መሪዎች ዓይነተኛ አብነት ናቸው፤ ፕሬዚደንት ሙጋቤ ሲጀምሩ የነጻነት ታጋይ አርበኛ ሆነው ነበር፤ በዚያን ጊዜ ሮዲዝያ በሚባለው አገር የሚኖሩ ነጮች የደቡብ አፍሪካ ነጮችን አብነት ተከትለው የነጮች የበላይነት የሰፈነበት አገዛዝ የዛሬ ሠላሳ ሦስት ዓመታት ግድም በጉልበት መሠረቱ፤ ሁለት የዚምባብዌ መሪዎች ጫካ ገቡና የትጥቅ ትግል ጀመሩ፤ የጎረቤት የአፍሪካ አገሮችና ሌሎችም እየረዱዋቸው ውጊያቸውን ቀጠሉ፤ እንግሊዞች ባዘጋቹት እርቅ የትጥቅ ትግሉ አብቅቶ ወደሰላማዊ የፖሊቲካ ትግል ገቡ።

የሰላማዊ የፖሊቲካ ትግሉን ቀደም ብለው ሲያካሂዱ የነበሩ ሙዜሬዋ የሚባሉ ጳጳስ የፖሊቲካ መሪ ነበሩ፤ ሙጋቤና ንኮሞ ከጫካ ከነወታደሮቻቸው ሲገቡ ጠመንጃ የበላይነትን እየያዘ መጣና ሙዜሬዋ ጫካ ባለመግባታቸው የነጮች አቀንቃኝ እየተባሉ ይዘለፉ ጀመረ፤ እርቁን ተከትሎ በተደረገው ምርጫ ሙጋቤ የበለጠ የሕዝብ ድምፅ አገኙና በሥልጣን ወንበሩ ላይ ወጡ፤ ነጮቹ በጣም ያለሙት ትልቅ አገር ለሙጋቤ፣ ለንኮሞና ለሙዜሬዋ አልበቃም አለ፤ ሙጋቤ ሁሉንም እየጠለፉ ጣሉና ሥልጣን የግሌ ነው ብለው ሙጭጭ አድርገው ያዙ።

በአፍሪካ ደረጃ ከፍተኛ የነበረው የልማት ሁኔታ ቀስ በቀስ እየወረደ የዚምባብዌ ሕዝብ በችጋር የሚጠቃበት ደረጃ ላይ ደረሰ፤ የነጮቹን ሰፋፊ እርሻ ለመከፋፈል የተወሰደው እርምጃ የሙጋቤን የማን አለብኝነት የጡንቻ አስተሳሰብ የሚያሳይ ነው፤ ሕዝቡ በነጮቹ እርሻ ላይ እንዲዘምትና እንዲዘርፍ አደረጉት፤ በመውደቅ ላይ የነበረው የአገሩ የልማት ሁኔታ መንኮታኮት ጀመረ፤ የዚምባብዌ ገንዘብ ክፉኛ ጥንቡን ጣለ፤ አንድ ዳቦ ለመግዛት ብዙ ብር መሸከም አስፈለገ፤ በሙጋቤ የጭካኔ አገዛዝ ምክንያት ምዕራባውያን መንግሥታት እየጮሁ በአገሩ ላይ የተጣለው የኢኮኖሚ ማዕቀብ ሕዝቡን በችጋርና በችግር አደማው፤ በዚያ ላይ ትንሽ ተቃውሞ የሚያሳየውን ሁሉ በጥይት እያነደዱ በጉልበት መንዳት ልማድ ሆነ፤ ጸጥ-ለጥ አድርጎ የመግዛት ዘዴና ልማድ ተስፋፋ።

ሕዝቡ መከራውና ችግሩ እያየለበት ሲሄድ በብዛት የተቃናቃኝ የፖሊቲካ ቡድኖችን መደገፍ ጀመረ፤ የአገዛዙ ቀኝ እጅ ከሆኑትም ውስጥ ወደተቀናቃኝ ጎራ ዞሩ፤ በተቀናቃኝ ቡድኑ ጎራ መሪ እንዳይኖር ለማድረግ ብዙ ተሞከረ፤ መሪውን ይዘው እንዳይሞት እንዳይሽር አድርገው ለቀቁት፤ ለጥቂት ጊዜ በደቡብ አፍሪካ ተጠልሎ ካገገመ በኋላ ተመለሰ፤ የምርጫውን ስርቆት አንድ ፖሊስ በስውር ካሜራ አንሥቶ ለቢቢሲ በመስጠት አጋልጦታል፤ ያም ሆኖ የተቀናቃኝ ቡድኑ መሪ አሸነፈ፤ሙጋቤ ግን ‹‹እንዴት ተብሎ!›› ብለው አማላጆችንም ሽማግሌዎችንም እያሳፈሩ መለሱ፤ በምርጫው ቢሸነፉም ፕሬዚደንት ሆነው እንዲቀጥሉና የተቀናቃኙ ቡድን መሪ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲሆን አስታራቂዎች ውለታ አስገብተዋቸው ነበር፤ ስምምነቱንም እስከዛሬ አላከበሩም።

ሰሞኑን ደግሞ የሙጋቤ የጭካኔ አገዛዝ ክፉኛ የሚጋለጥበት ነገር አጋጠመው፤ በአገሩ የውሀ ችግር በመከሰቱ ሰው ሁሉ ያገኘውን የተበከለ ውሀ እየጠጣ የኮሌራ በሽታ ተዛመተና ብዙ ሰዎችን ጨረሰ፤ አሁን ያለው ግምት ከአንድ ሺህ ሰዎች በላይ መሞታቸው ነው፤ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ደግሞ በሕመሙ እየተሰቃዩ ነው፤ ፕሬዚደንት ሙጋቤ ግን በአገራቸው የኮሌራ በሽታ ችግር እንደሌለ ይናገራሉ፤እሳቸው ዘንድ መቼም አይደርስምና በምን ይወቁት! በሽታው ግን ድንበር-ዘለል በመሆኑ ወደደቡብ አፍሪካ ጠረፍ ስለደረሰ የደቡብ አፍሪካ መንግሥት አካባቢውን የአደጋ ክልል በማለት አውጆ የህክምና ባለሙያዎችን ልኮ እየተከላከለ ይገኛል። በመካድ ችግሩን የሚያስወግዱት የሚመስላቸው የአፍሪካ መሪዎች ብዙ ናቸው።

ዓለም በሙሉ የሚጮህበት ብዙ ግፍ በሚሠራበት አገር አልፎ አልፎ አንዳንድ አስገራሚ ነገሮች ብቅ ይላሉ፤ እኔን ያስገረመኝ የአንድ ፖሊስ ታሪክ ነው፤ ሁኔታውን ሁሉ ከተመለከተ በኋላ የተቀናቃኙ የፖሊቲካ ቡድን አባል ይሆናል፤ ይያዝና ታስሮ ፍዳውን ይበላል፤ ከዚያም ከሥራው ይታገዳል፤ በፍርድ ቤት ክስ ይመሠርትና ይፈረድለታል፤ ከነበረበት ዝቅተኛ ሥራ ላይ ተመድቦ ዱሮ ከነበረው ደመወዝ ግማሽ ብቻ እያገኘ እንዲሠራ ይደረጋል፤ የዚምባብዌ ፍርድ ቤት የፖሊሱን መብት ማስከበሩ ያስገርማል።

በነጻነት ታጋይነት ወንበሩ ላይ የወጡት ሙጋቤ ዛሬ የነጻነት ጠላት ሆነው ከነጮቹ አገዛዝ ዘመን በከፋ ሁኔታ ውስጥ ጨምረውታል፤ ሆኖም ለዚምባብዌ ሕዝብ ፍርድ ቤት ካለ አንዱ የዚምባብዌ ስደተኛ ‹‹ሰው ሁሉ እየወጣ ድንጋይ ብቻ የሚቀርበት አገር ይሆናል›› ያለው ትክክል አይመስለኝም።